# ስግደት ለቅዱሳን (ለጻድቃን)

ለእግዚአብሔር የሚቀርበው የአምልኮ ስግደት ሲሆን ለእግዚአብሔር ወዳጆች የሚቀርበው ስግደት ግን
የአክብሮትና የልዕልና (ከፍ ከፍ የማድረግ) ስግደት ነው። በልደት ጊዜ ሰብአ ሰገል ለጌታችን ያቀረቡ
ት ስግደት የአምልኮ ስግደት ነው። ሰብአ ሰገል ለጌታችን ወድቀው የሰገዱለት ጌታችን አምላክ መሆኑ
ን ተረድተው ነው (ማቴ. 2፣11)። በዮሐንስ ወንጌል እንደ ተገለጸው ጌታችን የነገረን ስግደት የአምልኮ
ስግደት ነው (ዮሐ. 4፣23-24)።

ለቅዱሳን የሚቀርበው ስግደት ግን ከአክብሮትና ከፍቅር የተነሣ የሚቀርብ ነው። የዘመኑ ተከራካሪዎች
ስግደት ለእግዚአብሔር እንጂ ለጻድቃን፣ ለሰማዕታትና ለመላእክት መቅረብ የለበትም እያሉ በከንቱ ይ
ከራከራሉ።

በዮሐንስ ራእይ 7፣14 እንደ ተገለጸው በሰይፍም ሆነ በገድል፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ፈጣሪያቸው
ን ሲያገለግሉ ኖረው በሞት ወደ እግዚአብሔር ለሄዱ ቅዱሳን ቅዱስ አጽማቸው ባረፈበትና በስማቸው
ቤተ ክርስቲያን በታነጸበት በመገኘት የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት ማቅረብ የሚገባ ነው። ቅዱሳን በሕይወ
ተ ሥጋ (በአጸደ ሥጋ) ሳሉ የአክብሮት ስግደት ሲቀርብላቸው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል
። ይህንንም ለማወቅ ቀጥሎ የቀረበውን ማስረጃ እንመልከት፤

1ኛ/ የእስራኤል ንጉስ ከነበረው ከአካዝያስ አምሳ ወታደሮችን አስከትሎ የተላከው የአምሳ አለቃው ሰ
ው ወደ ነቢዩ ኤልያስ ሄዶ በፊቱ ቀረበ፤ በጉልበቱ ተንበረከከና «የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ ነፍሴና የ
እነዚህ የአምሳው ባሪያዎችህ ነፍስ በፊትህ የከበረች ትሁን» ብሎ ተንበርክኮ የሰገደለት መሆኑን መጽሀ
ፍ ቅዱስ በቀጥታ ያረጋግጣል (2ኛ ነገሥ. 1፤13)። ያ የአምሳ አለቃ ነቢዩን ኤልያስን በታላቅ አክብሮት
ተንበርክኮ ስለ ለመነው ነቢዩ ኤልያስ ጉዳዩን ፈጸመለት። ከእርሱ በፊት መጥተው የነበሩ ሁለት የአም
ሳ አለቆች ግን ያለ ምንም አክብሮት በትዕቢት ተሞልተው ነቢዩ ኤልያስን «ንጉሥ ይጠራሃልና ና ውረ
ድ» ብለው በጠየቁት ጊዜ በነቢዩ ጸሎት ከሰማይ በወረደች እሳት ተቃጥለው ሞተዋል (2ኛ ነገሥ. 1፤9
12)።

2ኛ/ ናቡከደነፆር በራእይ (በሕልም) ያየውን ራእይ የሚተረጉምለት አዋቂ አጥቶ ግራ ገብቶት ሳለ ሕል
ሙን ይፈታለት ዘንድ ዳንኤልን ፈልገው ወደ ንጉሡ አቀረቡትና እንዲህ አለው። «....ምስጢርን የሚገ
ልጥ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ....»። ይህንን ሲለው ንጉሡ ናቡከደነፆር ያየውን ሕልም በሙሉ ተረጐ
መለት። በዚያን ጊዜ ንጉሡ ናቡከደነፆር ወደ ዳንኤል ቀርቦ በግንባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት፤ የእ
ሉንም ቁርባን እጣኑንም ያቀርቡለት ዘንድ አዘዘ። ንጉሡም ዳንኤልን «ይህን ምስጢር ትገልጥ ዘንድ ተ
ችሎሃልና በእውነት አምላካችሁ የአማልክት አምላክ፤ የነገሥታትም ጌታ፤ ምስጢርም ገላጭ ነው» ብ
ሎ ነገረው (ዳን. 2፤25-48)።

ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው ንጉሡ ናቡከደነፆር ነቢዩ ዳንኤልን ያከበረውና ወድቆ የሰገደለት አምላክ
ነህ ብሎ አይደለም። ነገር ግን የአምላክ መልክተኛ መሆኑን በሚገባ ስለተገነዘበ ነው። እንደዚሁም ዳና
ኤልን ያንን ታላቅ ምስጢር ለመተርጐም የቻለው አምላክ የመረጠውና ያከበረው ሰው መሆኑን ተረድቶ
ነው።

ስለዚህ ንጉሡ ለዳንኤል ያቀረበው ስግደትም ሆነ ዕጣን ወይም የእህል ቁርባን የአክብሮት መሆኑን መገ
ንዘብ ይገባል።  ቤተ ክርስቲያንም በዚሁ መልክ የእግዚአብሔር ወዳጆች ለሆኑት ቅዱሳን አጽማቸው
ባረፈበት ስማቸው በተጠራበት ቦታ (ቤተ መቅደስ) ምእመናን በስማቸው ዕጣንና የእህል ቁርባን (ጠበል
ጸዲቅ) ከስግደት ጋር እንዲያቀርቡ ታስተምራለች። ስግደቱም ተደጋግሞ እንደተገለጸው የጸጋ ማለት የ
አክብሮት ስግደት ነው።

3ኛ/ ነቢዩ ኤልሳዕ ብዙ ተአምራት በእግዚአብሔር ስም አድርጎአል። ካደረጋቸው ተአምራት መካከል
አንደኛው ሙት ማስነሳት ነው። ሙቶ የተነሳውም የሱናማዊት ሴት ልጅ ነበር። ሱናማዊት ሴት ነቢዩን

እየተቀበለች በቤትዋ ታስተናግደው ነበር። ከባልዋም ጋር ሆና የነቢዩን በረከት ትቀበል ነበር። ስለዚህ በነቢዩ ኤልሳዕ ጸሎት ልጅ ወለደች፤ ሆኖም ሕጻኑ ካደገ በኋላ ታመመና ሞተ። ነቢዩ ኤልሳዕ ግን ሴትዮዋን በማጽናናት በሬሳው ላይ ሰባት ጊዜ ጸለየበት፤ በመጨረሻም ነቢዩ በእግዚአብሔር ኃይል የሞተውን ልጅ አስነሳውና ለእናቱ ሰጣት። ሴትዮዋም ወደ ነቢዩ ማረፊያ ገብታ በአጠገቡ በምድር ላይ ተደፍታ ሰገደችለት። ልጅዋንም ይዛ ሄደች (2ኛ ነገስ. 4፤8-37)።

4ኛ/ በዘመነ ሐዲስም የእግዚአብሔር ወዳጆች ለሆኑት የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት ይቀርብላቸው ነበር። ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ወንጌልን በማስተማራቸው በወህኒ ቤት እንዲታሰሩ ተፈረደባቸው። በእስር ቤት ታስረው በመንፈቀ ሌሊት ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ፤ የወህኒ ቤቱ መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የመሬት መናወጥ (መንቀጥቀጥ) መሆኑን ያየና የተመለከተ የወህኒ ቤቱ ኃላፊ ወደ እነ ጳውሎስ ቀርቦ በግንባሩ ተደፋ (ሰገደ)። ወደ ውጭ አወጣቸውና «ጌቶቼ ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? » አላቸው። እነርሱም «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ» አሉት (የሐዋ. 16፤ 25-34)።

ይህ የወህኒ ቤት ኃላፊ ጳውሎስና ሲላስ ሰዎች መሆናቸውን አውቆአል። አምላክም አለመሆናቸውን ተረድቶአል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ወዳጆችና አገልጋዮች መሆናቸውን በሠሩት ተአምራት አማካይነት ስለ ተረዳ «ጌቶቼ» ብሎ በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደላቸው፤ የድኅነትንም መንገድ ጠየቃቸው። እነርሱም የድኅነት መንገድ (የሕይወት መንገድ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አመለከቱት (ዮሐ. 14፤1-5)።

ስግደት እንኳንስ እግዚአብሔር ለመረጣቸው ለቅዱሳን ይቅርና ለባለሥልጣን፤ በዕድሜ ለሚበልጥ ሰውና ለሽማግሌ ሁሉ እንደሚቀርብ የታወቀ አይደለምን? ራስን አዘንብሎ እጅ መንሣት ከስግደት ጋር ግንኙነት ያለው አይደለም? ዔሳውና ያዕቆብ በተገናኙ ጊዜ ያዕቆብ ወንድሙን ዔሳውን በማክበር ሰባት ጊዜ እንደ ሰገደለት መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል (ዘፍ. 33፤1-4)። እስራኤላውያንም ተሰብስበው ለንጉስ የሚገባውን ስግደት ለንጉሡ፤ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ስግደት ለእግዚአብሔር እንዳቀረቡ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ኛ ዜና. 29፤20-21)

ስለዚህ እግዚአብሔርን አገልግለው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነው ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ለተለዩ ቅዱሳን ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል እያልን እናመሰግናቸዋለን (ሮሜ. 2፤10)። ቅዱሳን በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለው ክርስቶስን ለብሰው ሆነውና (ገላ. 3፤27) እሱን አገልግለው በሞት ወደ እርሱ ሲሄዱ፤ ቅዱስ አጽማቸው እግዚአብሔር የባረከው በመሆኑ፤ ድውይ ይፈውሳል፤ሙት ያስነሳል (ነገ. 13፤20)፤ ሌላም ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ይሠራል። በዚሁ መሠረት የእግዚአብሔር ወዳጆችና አገልጋዮች የሆኑትን ቅዱሳን የሚያከብር ሁሉ በቅዱሳን ጸሎትና አማላጅነት ከእግዚአብሔር ክብርን በረከትን ይቀበላል።

ቅዱሳን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ግማሾቹ በሰማዕትነት ስለ ክርስቶስ ደማቸውን አፍስሰውና መስዋዕት በመሆን፤ ሌሎቹም በዱር በገደል በጾም፣ በጸሎትና በስግደት ሕይወታቸውን አሳልፈው በመስጠት በአካለ ነፍስ (በነፍሳቸው) ወደ ጌታችን ሄደው በመንበሩ ዙሪያ ሆነው ቀንና ሌሊት እርሱን ሲያመሰግኑ እንደሚኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፤ እንደዚሁም ሲጸልዩ እንደሚኖሩ ያስረዳናል። (ራእይ 6፤9 ፣ 7፤ 14- 17)።

ስለዚህ ቅዱሳንን ራሱ እግዚአብሔር ስለ መረጣቸውና ስላከበራቸው (ሮሜ. 8፤ 34) እኛ ሁላችን ልናከብራቸውና የጸጋ (የአክብሮት) ስግደትም ልናቀርብላቸው ይገባናል።

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በ1990 «ክብረ ቅዱሳን» በሚል ርእስ ካዘጋጁት መጽሐፍ የተወሰደ።

.